የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ህዳር ፳ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 8
ADDIS ABABA, 30th November, 2023


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፪/፪ሺ፲፮

ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የኢትዮጵያን የቡና እሴት ሰንሰለት ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ…………………………………. ገጽ ፲፭ሺ፪፻፹፫


**Content**


Proclamation No. 1302/2023

Italian Republic Loan Agreement for financing Support Ethiopian agribusiness development operating in the coffee value chain, through de-risking investments and institutional support to the Ethiopian Coffee and Tea Authority Project Ratification Proclamation…………..Page 15283


**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፪/፪ሺ፲፮**

**<u>በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የኢትዮጵያን የቡና እሴት ሰንሰለት ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል አስር ሚሊዮን ዩሮ (፲ ሚሊዮን ዩሮ) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

**PROCLAMATION NO. 1302/2023**

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF ITALIAN REPUBLIC</u>**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic stipulating that the Government of the Italian Republic shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to ten million Euro (Euro 10,000,000.00) for financing Support Ethiopian agribusiness development operating in the coffee value chain, through de-risking investments and institutional support to the Ethiopian Coffee and Tea Authority Project, was signed in Addis Ababa on 9th Day of March, 2023;

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ፫ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ጥቅምት ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፩ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የኢትዮጵያን የቡና እሴት ሰንሰለት ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፪/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር F.ROT/AID 22/001/00 በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን አስር ሚሊዮን ዩሮ (፲ ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of The Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 3rd year working period, 1st ordinary session held on 12th Day of October, 2023;

**NOW,THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Italian Republic Loan Agreement for financing Support Ethiopian agribusiness development operating in the coffee value chain, through de-risking investments and institutional support to the Ethiopian Coffee and Tea Authority Project Ratification Proclamation No. 1302/2023".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number F.ROT/AID 22/001/00 signed in Addis Ababa on 9th Day of March, 2023 between The Government of The Federal Democratic Republic of Ethiopia and The Government of the Italian Republic is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan an amount equivalent to Ten Million Euros (Euro 10,000,000.00) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፳ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 30th Day of November, 2023**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**